
# የድሆች ጠበቃ!!



ጎመራው ኀይሉ ነው ፣ ኀይሉም ጎመራው ነው፣

ኀይሉ የተሰጠው ፣ ከእናት አባቱ ነው፣

መለያ መጠሪያው ስሙ የፀደቀ ነው፣

በስሙ ይጠራል ሁሌም ይታወሳል፣

ኀይሉ ሃይላችን ነው ሞዜርን ተኩሷል፣

ብዕሩ መድፍ ነው፣ የጠላት ቤት አፍርሷል፣

ዕውቀት አስጨብጦ ፣ የዐይን ብርሃን ገልጧል፣

ለትውልድ የሚቀር ፣ ትልቅ ሥራ ሰርቷል።

የዘራህው ፍሬ ፣ እሸቱ ሲያፈራ፣

ጎሞራው ወዴት ሄድክ ፣ ምን ብዬ ልጣራ፣

ያመድፈኛው ብዕርህ ፣ ሁሌ የማያባራ፣

ተኩሶ አነጣጥሮ ፣ ጠላት የሚያስጓራ፣

ብትንትን አድርጎ ፣ የሚያደርግ አቧራ።

እኮ የታል ጋሼ ፣ የኛ ኀይሉ ጎሞራ?

ሞቾትን ሳትሻ ፣ እኔ ይድላኝ ሳትል፣

ዓለምን ንቀሃት ፣ ላባደሩን ስትል፣

ዓለምን ንቀሃት ፣ አርሶ አደሩን ስትል፣

በልቶ ላላደረው ፣ ለታረዘው ስትል፣

እምቢ አሻፈረኝ ፣ ከርሳም ይውደም ብለህ፣

ለዓለም ሳትበገር ፣ መደሰት ሳያምርህ ፣

መሰናበትህ ነው ፣ ጋሼ ውነት ከምርህ ፣

ፒያሳ አራትኪሎን ፣ አራዳን ስንጎባኝ፣

ያን የቆምክለትክን ፣ ሕዝብህን ሳታገኝ፣

ባንቢስ ገብርኤልን፣ ዑራኤልን ሳናይ፣

የዘራህውን ፍሬ ፣ ማበቡንም ሳታይ፣

የተወለድክባትን ፣ ኢትዮጵያን ሳትጎበኝ፣

መሰናበትህ ነው ፣ ብለህ ዓለም በቃኝ።

ወያኔን አዋርደን ፣ ሱሩ አስወልቀን፣

በንብርክክ አስኪደን ፣ ጉልበትክን አስመን፣

እስጢፋኖስ ደርሰን ፣ ቤተ እግዚአብሔር ስመን፣

ያለፉትን ጀግኖች ፣ ሰላምታ ሳንሰጥ፣

ኀይሉ ፈጠንክብን ፣ ከኞ እንዴት አመለጥክ፣

ኀይሉ ፈጠንክብን ፣ ከኞ እንዴት አመለጥክ።

መይሳው ከምድረ ስዊድን

2014-12-13

መቼም ያንተ ጥሩነት ተነግሮ አያልቅም

አንዱ ጓደኛችን በጻፈው መጽሃፍ እንዲህ ይነበባል

” … My heartfelt thanks also goes to my mentor, my teacher and the livning legend,

Novelist Laureate Hailu Gebre Yohannes, who took me in mind and body through a long journey of learning the African, Oriental, and Western cultures and market. His masteries of many languages, his ability to capture and poetically paint the beauties of nature and humanity, his depth of knowledge and interest in geophysics dealing with seismology and geodesy, all are appealing to me. His engaging discussion on development philosophy and logic have heightened my perception beyond the level of mere knowledge and to recognize the dynamic and turbulent episodes taking place in the wombs of the earth and the links human beings make to nature. His numerous scripts and literary works have encouraged me to open up my eyes,

Unveil and understand the contextual links between humanity and nature … “

ከዚሁ ጓደኛችን ጋር አብረን ስንሄድ ጻፉ ብለህ ያበረታታህኝን አልረሳውም!! ብዙ ማለት ይቻል ነበር ግን ይሄ ይበቃል፣ ከበሃር ውስጥ በጭልፋ እንደመጨለፍ ነው ስላንተ በዚህ ግጥም ለመግለጽ መሞከር።